# የዐማራ ኅልውና ቃል-ኪዳን

**ግንቦት ፪ ሺህ ፲፩ ዓ/ም**

*“የዐማራ ኅልዉና ቃል-ኪዳን” ባለፉት ሁለት ትውልዶች የዐማራ ሕዝብ እንደ ሕዝብ የገጠሙትን የኅልውና ተግዳሮቶች በሚገባ አስገንዝቦ አብረው የመጡ ዕድሎችን ለመጠቀም፣ አደጋዎችንም ለመቋቋም የሚያስችሉ ስልቶችን የሚጠቁም አቅጣጫ ሰጭ ሰነድ ነው። በዘመን ተሻጋሪ የወል እይታ የዐማራ ሕዝብ ማንነትን፣ ዕጣ-ፈንታውንና ሰቆቃ የወለደውን ንቃተ-ኅሊና በተጨባጭነት ይተርካል። በተለይም የዚህን ትልቅና ታላቅ ሕዝብ ታሪካዊነት፣ አኩሪ ስልጣኔ፣አብነታዊ እሴቶች፣ የፖለቲካ ማንነትና መሠረታዊ ጥቅሞችን ጨምቆ ያቀርባል። ስለዚህም ዐማራዊ ድርጅቶችም ሆኑ ንቅናቄዎች የሕዝቡን ርቀተ-ሰፊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅሞችን አገናዝበው፤* ***“ዐማራነት መነሻችን፣ ኢትዮጵያዊነት መዳረሻችን”*** *በሚል ብሒል እንዲታገሉ የሚረዳ የወል ራዕይን ይነድፋል። በተለይም በቅርቡ በፌደራል መንግስት የታዎጀበትን ጦርነት በዘላቂነት ለማሸነፍ ጠንካራ ድርጅትንና መሪዎች ማፍራት፣ ፍሬያማ ስልቶችንና ከመስዋዕትነት በኋላ ለሚገነባው ነጻና የበለጸገ ህብረተሰብ ፍኖተ-ካርታ እንዲነደፍም አቅጣቻዎችና አስቸኳይ ጥሪ ያቀርባል።*

*በቃል ኪዳኑ የተካተቱት ‹የከየት፣ወዴት፣ ለምንና የእንዴት› ጥያቄዎችና መልሶች ሲጨመቁ የሚከተሉትን አምስት ፍሬ ሃሳቦችን ያነግባሉ፡- (፩ኛ) ዐማራ ድህረ-ዘውጌ ስርዓትን ቀደም ብሎ የተጎናጸፈ ሕዝብ በመሆኑ፣ አሁን ወደታች ወርዶ በተኮረጀ ‘እኛና-እነሱ’ ፖለቲካ እራሱን ለማሰለፍ ስነልቦናው ስለማይፈቅድለት ስለውስጥ ጠላቶች ባህርይ ተደናግሮ ቆይቷል፤(፪ኛ) ዐማራ የኢትዮጵያን ሃገረ-መንግሥት በመሪነት በመገንባት ሰንደቋን ለሰባት መቶ አመታት ያነገቡ መሪዎችን ማፍራቱ ትልቅ ትሩፋቶቹ ናቸው፤ (፫ኛ) በአይበገሬነቱና ባቃፊነቱ የውጭ ጠላቶችና በቅርቡ እንዳሸን በፈሉ የውስጥ ፀረ-ኢትዮጵያ ጠላቶችም ጭምር በጅምላ ተፈርጆ፣ የመዋረድ፣ የመፈናቀልና፣ የማያባራ የዘር ማጽዳትና ማጥፋት ጥቃቶች ሲፈጸሙበት የቆየ ሆደ-ሰፊ ሕዝብ ነው፤ (፬ኛ) ዐማራ ሲነቃ የራሱን የማያስነጥቅ፣ የሌሎችንም የማይከጅል ሕዝብ በመሆኑ፣ ከኢትዮጵያን አጋሮቹ ጋር በነጻ ዜግነት ላይ የተመሰረተች እውነተኛ ዴሞክራሲያዊት እትዮጵያን መገንባት ትልቅ ምኞቱና ግቡ ነው፤ ብሎም (፭ኛ) ዐማራ-ተኮር የትግል ድርጅቶችና ንቅናቄዎች ተናበውና ተቀናጅተው እንዲሰሩ የጋራ ራዕይና ፍኖተ-ካርታን አመላካች ቃልኪዳን ስላስፈለጋቸው ይህ ሰነድ እንዚህን ፍላጎቶች ለሟሟላት የተዘጋጀ ነው።*

## (1) ዐማራ ዛሬ፡-ከየት እንደመጣህ፣ ወዴት እንደምትሄድ፣ እንዴትም እንደምትጓዝ ጠንቅቀህ እወቅ

ኢትዮጵያ ከሰማኒያ በላይ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙባትና ሦስቱን (ኦሪታዊ፣ ክርስትናና እስልምና) ሐይማኖቶችና ባኅላዊ እምነቶችን የሚከተሉ ዜጎቿ ከመቻቻል አልፈው ለዘመናት በፍቅር የኖሩባት ታሪካዊ አገር ናት። በተለይም ሁለት ተመጣጣኝ ነገዶች (ማለት ዐማራና ኦሮሞ) የአገሪቱን ሁለት-ሦስተኛ የሕዝብ ቁጥር የያዙባት ምድር ናት። ከዐማራ ተወላጅ አንድ-አምስተኛው ዛሬ ዐማራ ክልል ተብሎ ከሚጠራው መስተዳደር ውጭ፣ በተለይም በከተሞች በብዛት ይገኛል። እንዲሁም ከሰባት ዐማሮች አንዱ የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ነው።

ዛሬ ወሎና ሸዋ ከሚባሉት ክፍለ-አገራት፣ በተለይም “አምሃራ” ከሚባለው ጥንታዊ ግዛት ፈለቀ የሚባለው **ዐማራ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ታላቅ ባለ-ውለታ ሕዝብ ነው።** ከዐማራ ባኅሪዎች ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያህል፤

- የፖለቲካዊ ማንነቱን በዘር ግንድ የማያሰላ፤ በተለይም ከአገው፣ ትግሬ፣ አፋር፣ኦሮሞ፣ ጉራጌና አርጎባ ነገዶች ጋር የተዋለደ ሕዝብ ነው።
- የተለያዩ ጠቃሚ ባኅሎችንና እሴቶችን በማጣጣም ተቀብሎ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትን አላብሶ ለማበልጸግና ለማውረስ ትልቅ ተሰጥዖ ያለው ሕዝብ ነው። ለዚህም እንደማስረጃነት የኦርቶዶክስ፣ የሱኒ እስላም፣ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ እምነቶቻችን ከመጡባቸው ቦታዎች እንዴት እንደሚለዩ ማጤንና እንዲሁም አማርኛ ከአባቱ ከግዕዝና ሴሜቲክ ካልሆኑ ቋንቋዎቻችን ማካተቱን መጥቀስ በቂ ናቸው።
- በአቃፊነቱና አስተናጋጅነቱ ኢትዮጵያ በዓለም አሉ ከሚባሉት የሥልጣኔ ምንጮች እንድትቆጠርና የብዙኅንነት ተምሳሌት እንድትሆን በማድረግ ረገድም በግንባር-ቀደም የሚጠቀስ ሕዝብ ነው። እንደዛሬ አያድርገውና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ካገሩ ሲወጣ ተሰዶና ተንገላቶ ሣይሆን ኮርቶና ተከብሮ የመኖር ሥነ-ልቦናን እንዲጎናጸፍ ያስቻለው አንዱ የዚኽ ሕዝብ ትሩፋት ነው።
- የዐማራ ሕዝብ እኩልነትንና የዜግነት ዲሞክራሲን የሚያቅፍ ባህል ስላለው፤ አግላይነትንና ደካማን ማጥቃት ከልምዱና ከኃይማኖታዊ እሴቶቹ ተነስቶ የሚጸየፋቸው ባዕዳዊ ገጸ-ባኅሪያት ናቸው።

በዘይቤያዊ የፖለቲካ ቋንቋ “ዐማራ” ተብሎ የሚጠራውና ራሱን ግን በትውልድ አገሩ፣ ደብሩ፣ ሐይማኖቱ ወይንም በኢትዮጵያዊ ማንነቱ እስካሁን የሚገልጸው ይኽ ታላቅና ትልቅ ሕዝብ በአቃፊ ሥነ-ልቦናውና በዘርፈ-ብዙ የዘር ግንዱ ምክያት ላለፉት ፺፻ /ሰባት-መቶ/ ዓመታት የሃገረ-መንግሥት ሰንደቅ-ዓላማ አንጋቢ በመሆንና ዘመናዊ ሥልጣኔን የሚያዳብሩ (ማለት አብራሃማዊ ሐይማኖቶችን፣ አልባሳትን፣ የምግብ ባልትናን፣ ሥነ-ጽሑፍን፣ የወንድና የሴት እኩልነትንና እንዲሁም ዛሬ ሰማኒያ-ከመቶ በላይ ዜጋ የሚናገረውን አማርኛ ቋንቋን) የትብብር ዋልታዎችን ለብቻው ሣይሆን በመሪነት አበርክቷል። በሃያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ዘግይቶ ለተጀመረው የዘመናዊ አገር ግንባታ ደግሞ በዘውዱ ሥርዓት አድልያን የገቱና ችሎታን ያጎሉ የወታደርና የሲቪል አገልግሎቶችን፣ የትምሕርት፣ የንግድና የፍትኅ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ለአፍሪቃ አገሮች ምሳሌነቱን አስመስክሯል።

የዐማራ ተወላጅና መሰሎቹ ከብዙ በጥቂቱ በነእዚህ እሴቶቻቸው ይታወቃሉ፡-

- ፈሪኀ-እግዜአብሔርነት፣ ታታሪነት፣ ትኅትና፣ አብሮነት፣ ለራስና ለአገር ክብር መስጠት፤
- የጋራ ምኞቱም የዜግነት ክብሩና መብቱ ተጠብቆ፣ በላቡ ያፈራውን ሃብት ማስከበር፣ ሳይደርሱበት አለመድረስ፣ ከደረሱበት በሕግ መክሰስ፤ ፍትኅዊ ዳኝነት ሲነፈግና አማራጭ ሲያጣ መሸፈት የሚቀናው፣ እንዲሁም እንግዳን ቤት-ለእግዚአብሔር በማለት የሚያስተናግድ ሕዝብ ነው።

ስለዚህ በዐማራ ሕዝብ ስም የሚንቀሳቀሱ ስብስቦች፣ ድርጅቶችና ንቅናቄዎች በተልዕኳቸውም ሆነ በዓላማዎቻቸው ኋላ-ቀር የሆኑ ባኅሎችን ትተው ወደ ዘመናዊ ስርዓት የሚያሸጋግሩንን እሴቶችን (ማለት እኩልነት፣ ነፃነት፣ ተሳታፊነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነት፣ ሃቀኛነት፣ ሕግ-አክባሪነት) ማቀፍና በግብር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

## (2) ዐማራ ዛሬ፡-የፖለቲካ ራዕያችንና ተልዕኳችን በዐማራ እሴቶች ላይ መመስረት አለባቸው

በአሁኑ ጊዜ፣ ከፖለቲካ ባህላችን ጋር ምንም ዝምድና የሌለው "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" የሚባለው ፍጹማዊ ርዕዮተ አለም፣ አቃፊ የፖለቲካ ባህላችንን እንደማዘመን አዋርዶ፣ በዘር በተማከለ የከፋፍለህ-ግዛ አስተዳደራዊ ስልትንና መርሕን ያቀፈ አፋኝ አውታር ተዘርግቷል። ይህ ሥርዓት ደግሞ መዋቅራዊ ብዝበዛንና አምባገነትን እንጅ ዲሞክራሲያዊነትንም ሆነ አብዮታዊነትን እንደማያቅፍ ለሁለት ትውልድ በግብር ታይቷል። በማንነት ላይ የተመሰረተው ስርዓት ሕገመንግስታዊነትን ተጎናጽፎ በፊት በትግራዊ አቀንቃኞች አሁን ደግሞ በኦሮሙማ አቀንቃኞች ለጥቅምና ለስልጣን ማራዘሚያ ሲባል የታቀፈ አደገኛ ቦምብ ሆኖ ቆይቷል። እየፈነዳም ይገኛል።

ፍሬያማ ጅማሮዎችንና ስኬቶችን ያንቋሸሹ ኮራጅ ጎጠኞች ዐማራውን በጅምላ "ጨቋኝ ሕዝብ" ብለው በመፈረጅ፣ ከአብራኩ የወጡ ልጆቹን ጨምሮ በድንቁርና ወይንም በጥቅማዊነት ሲያስጠቁት ቆይተዋል። ለአብነት እታች የተጠቀሱት ክስተቶች የሚያመላክቱት የማንነት ፖለቲካ ከአገሪቱ ምድር እስካልጠፋ ድረስ ሁላችንንም በእኩልነት የምታቅፍ ዘመናዊ ኢትዮጵያን ለመጎናጸፍ የማንችል መሆናችንን ነው፡-

- ቀደም ሲል መሬት ለአራሹ በሚል መፈክር አሁን ደግሞ መሬትን ከማንነት ጋር በማጣመር ዐማራም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ርስቱን በህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ተነፍጎ፤ ዛሬ የመንግሥት ጭሰኛ ሆኖ መሬትም የገዥውን ፓርቲ የፖለቲካ ተልእኮ ማስፈጸሚያ መሳሪያ ተደርጓል፤
- ዐማራው ለብዙ ትውልዶች ከኖረባቸው ቀየዎች "መጤ" የሚል መለያ ተለጥፎበት አሁን ድረስ ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ በጅምላ እየተፈናቀለና አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ እየተፈጸመበት ይገኛል፤
- ቋንቋን/ዘርን መሠረት ባደረጉ የዘውግ ፓርቲዎችና ክልላዊ አስተዳደሮች እንደ-ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም ለይስሙላ በሕገመንግስቱ የተካተቱን መብቶቹን ተነጥቆ፣ ልጆቹንም በአማርኛ እንዳያስተምርና በብሔራዊ ቋንቋው እንዳይዳኝ እገዳ ተጥሎበት እየተንገላታ ይገኛል፤
- በዐማራ ክልል ተብየውም በድህነትና የመሰረተ-ልማት እጦት አንደኛ ማዕረግን ታቅፎ፣ ችግሩን እንዳያሰማ ቅቡልነትና አመኔታ ባላቸው መሪዎች እንዳይተዳደር፣ እንዲሁም ቁጥሩ ሆን ብሎ ተቀንሶ የሚገባውን በጀት እንዳያገኝ ተደርጎ ቆይቷል፤
- እንዲሁም የዐማራ ተወላጆች አድልዖ ሣይደረግባቸው የትምሕርት፣ የንግድ እንዲሁም በፌዴራል መሥሪያ-ቤቶች የመሥራት ዕድልና ፍትኀ እንዳያገኙ በተሸረቡ ሴራዎች ሰለባ ሆነዋል፤
- ባለፉት ሁለት አመታት ወያኔ/ሕወሐትና ኦነግ በዐማራ ሕብረተሰብ ላይ በይፋና በተጓዳኝ ዘዴዎች ተደጋጋሚ እልቂቶችና ዘረፋዎች ሲፈጸሙ መንግሥታዊ የጸጥታ ኃይሎች ስልታዊ ማፈግፈግ፣ እንዲሁም ጽንፈኞች ጥቃት ከመፈጸማቸው በፊት አይቶ እንዳላየ ከቦታዎቹ ሆን ብሎ በመውጣትና ከጥቃቱ በኋላ ደግሞ የአዞ-እንባ በማፍሰስ ደባዎችን ከተላመድን አመታት አልፈዋል፤
- ዘርፈ-ብዙው ጭቆና መንግሥት-መር፣ ስርዓታዊና መዋቅራዊ በመሆኑ ዐማራው ለማን አቤቱታ እንደሚያቀርብ ግራ ገብቶት ቆይቶ ተስፋው ሲመነምን እነሆ ዛሬ እንደ ሕዝብ ወደ ራስህን-አድን ጥሪ ፊቱን እንዲያዞር ተገድዷል።

ስልጡንና ሆደ-ሰፊ ሕዝብ በመዘናጋትና በበቂነት ባለመደራጀት፣ በመንጋ አረመኔአዊ ኃይሎች ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንደሚሸነፍ የኛም የዓለምም ታሪክ በግልጽ ያሳያል። የዐማራው ሕዝብ እነዚህን የመሰሉ ዘግናኝ ጥቃቶችና ወንጀሎች ቢያንስ ለሃምሳ ዓመታት ሲፈጽሙበት፣ በአንድ ገጹ ለአገር አንድነት ሲባል ተመስጋኝ ሰፊ ትዕግስትን ቢያሳይም በሌላ ገጹ ደግሞ አደጋውን ዘግይቶ የመገንዘብ ዝንጉነትን አሳይቷል። አርቆ ማየት እንደ-ፈሪነትና ሞኝነት ተወስዶ በትንሹም በትልቁም መስዋዕተኛ ተደርጎ፣ አይንህን ላፈር ተብሎ፣ የጥቃት ዒላማ ሆኖ በትንሹም በትልቁም እየተዘመተበት ይገኛል።

የኢትዮጵያ መንግሥታዊ አውታር በፀረ-አንድነት ጎጠኛ ኃይሎች ከተጠለፈ በኋላ፣ በአይደፈሬነቱ ይቋቋመናል በሚል ፍራቻ ጥላ ስር ያለው የዐማራ ሕዝብ፣ ከሻቢያ ጀምሮ እስከዛሬው ብልጽግናና ኦነግ ድረስ ከፋኖ እስከ ቀሳውስት የጥቃት ዒላማ ሆኖ መታደኑ ቀጥሏል። ጎልውና ላይ ያተኮረ እኩይ ተግባር ተደጋግሞ ሲፈጸምና ወደፊትም እንደሚቀጥል ከታወቀ በኋላ፣ ፊትን ሸፍኖ ልከት በሌለው ቸልተኝነት መታገስ ኢትዮጵያን ለመታደግ ቀርቶ እራሱን ዐማራውን ወዳለመኖር እንደሚወስደው ግልጽ ሆኖ የመጣ እውነታ ነው። ሞኝን ልጅ እናቱም አትወደውም እንዲሉ፣ ዐማራው ተነጥሎ ለተለያዩ ዘግናኝ ጥቃቶች በተዳረገበት በዚኽ የከፋ ጊዜ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ በሚጠበቀው ደረጃ አብረውት ቆመው አይታዩም። በተለያየ ጊዜ የዘረኛው ስርዓት አፈና ሰለባ የሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንም በጋራ መታገልና ከዐማራው ሕዝብ ጋር ያሏቸውን አገራዊ ትስስሮች በማደስ በአጋርነት መቆም የነሱም የዐማራውም አንገብጋቢ ግዳጅ ነው። በስማቸው የጽንፈኛ ድርጊት የሚፈጸምባቸውም ነግ በኔ ብለው ድምጻቸውን ማሰማት ግዴታቸው ነው።

## (3) ስልታዊ ግንዛቤዎች

በኢሕአዴግ የውስጥ ፉክቻ ላይ ያተኮረው የተረኝነት የሥልጣን ቅብብል እንደምኞታችን ኢትዮጵያን ከዘዉግ ክፍፍል ለማዉጣት ፋይዳ እንደሌለው ያለፉት አምስት ዓመታት በግልጽ አሳይተዋል። የማዕከላዊና የክልላዊ መንግሥታት አስተዳደራዊ፣ ወታደራዊና የፀጥታ መዋቅሮችን የጠለፉት የኦሮሙማና ኦነጋዊ የሥልጣን ጥመኞች የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት፣ የአገርን አንድነትና ዳር-ድንበር የማስከበር ፍላጎት አጥተው አገሪቱን ለከፋ አደጋ አጋልጠዋታል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሕዝባዊና ኢመደበኛ ታጣቂዎችን በማሰልጠን ለእርስ በርስ ጦርነትና ለማፊያ ዝርፊያ አገሪቱ እየተመቻቸች ነው። መሪ-አልባ የሆነው ዐማራና ሌሎች የአንድነት ኃይሎች በጋራ መቆም ተስኗቸው፣ የጎልውና ዋስትና በሚያጡበት ጎዳና እየተነዱ፣ በፈረቃ ለጅምላ መፈናቀል፣ ለዘርፈ-ብዙ ሰቆቃና ለዘግናኝ የዘር-ማጥፋት ግድያ ተጋልጠው ይገኛሉ።

ዐማራው በብዛት የሚኖርባቸው ኅብረ-ብሔራዊ ከተሞች (በተለይም አዲስ-አበባና አካባቢዋ፣ ድሬዳዋ፣ ናዝሬት፣ ሐረር፣ አሰላና አዋሳ) መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ጽንፈኞች በአደባባይ የሚዘርፉባቸው፣ ንጹኅን ዜጎች የሚፈናቀሉባቸውና ካለ-ጠያቂ የሚገደሉባቸው ማዕከላት ሆነዋል። በወልቃይት፣ጠገዴ፣ ደራ፣ መተከል፣ ራያ፣ ወለጋ፣ ጉራፈርዳ፣ሻሸመኔ፣ ሓረር፣ ሶማሌ ክልል፣ ከሚሴና ጋምቤላ እንደታየው፣ አብዛኛዎቹ ክፍሎች የሁከት፣ የዘር ማጽጂያ/ማጥፊያና የመሬት ቅርምት መስክ ሆነዋል።

እንዲንሰራፉ የተፈቀደለት ይኽ አደገኛ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት በታሪካችን ከግራኝና ከጣሊያን ወረራዎች ጊዜ ውጭ ታይቶ የማይታወቅ፣ አገር-አጥፊ ተግባር እንደሆነ፣ ሕዝብንም እጅግ ለከፋ ሰቆቃና ትርምስ እንደሚዳርግ ሊታወቅ ይገባል። ስለሆነም፣ የጋራ አገራችን በአንድነት እንድትቀጥል፣ ሕዝብም ሰላሙን እንዲያገኝ ችግሩ የሚያስከትለውን መዘዝ የተረዱ ሁሉ ተባብረው ይኽን እኩይ ስርዓት ሊቀለብሱት ያስፈልጋል፣ ይገባልም።

ባጭሩ ዐማራው በዓለም-አቀፍ የተደነገጉ ሰብዓዊና ዜጋዊ መብቶቹ ብቻ ሣይሆኑ እንደ-ማኅበረሰብ ጎልውናው ጭምር በወያኔው ነቀርሣዊ ሕገ-መንግሥት ጥላ ስር ፍጹም ሊከበሩ አልቻሉም፤ አይችሉምም። በሥልጣን

ለመቆየት ከአሳዳጊዉ ሕወሐት እንደተማረዉ፣ ሁሉንም ጠቅልሎና አፍኖ በብቸኝነት የያዘና ወደ አፈናዊ አስተዳደር የዘቀጠ ገዢ-ፓርቲ በሚያካሂደው የአስመሳይ ለውጥ ማዕቀፍ ጭቆና ያከትማል፣ ብልጽግና ይመጣል ብሎ ማሰብ ከቅዠት አያልፍም። ስለዚህ ለዐማራ ኅልውናና አርነት፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲሁም ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ሥርዓት ቆመናል የሚሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አዲስ የመዋቅራዊ አድማስ ለመክፈት የሚያስችል የእርቀ-ሰላምና ሁሉን አቃፊ የሽግግር ድርድር ሂደት አስፈላጊነትን መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል።

ዐማራን ከድቶ ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ማለት ታሪክ ይቅርታ የማያደርግለት ግብዝነት ነው። በአንድ እጅ ብቻ አይጨበጨብም እንደሚባለው ዐማራ በምሰሶነት የገነባትን ሁሉን ያቀፈች ኢትዮጵያን ብቻውን ሊታደጋት አይችልም። የማንነቱ መሠረት ስለሆነች ደግሞ ሊረሳትም ከቶ አይችልም። አበው እንደሚሉት "መከበር ከመፈቀር ወይንም ከመፈራት" ከመነጨ፣ ሁሉም ዘውጌኛ ለእርስ-በርስ ጦርነት እየተዘጋጀ እያዩ እጅን አጣጥፎና ፈዝዞ መቀመጥ በእሳት ሊጋይ የተለኮሰን ቤት ለማጽዳት ከመከጀልና እራስን ለማያቋርጥ ሰቆቃ ለመዳረግ ከመፈለግ ተለይቶ አይታይም።

በቸልተኝነት፣ በግብዝነትም ሆነ በፍራቻ ተለጉሞ መጠቃት አማራነት ሣይሆን ከገልቱነት አልፎ ኅሊና-ቢስነት ይሆናል፤ ዐማራነትንም ኢትዮጵያዊነትንም አይመጥንም። ስለዚህ፣ እራስን ከሴረኛም ሆነ ከአረመኔአዊ መንጋ ከሚሰነዘር ጥቃት ለመቋቋም ሰፊ ድርጅታዊ መረብ መዘርጋትና ወዳጆችን ማብዛት የወቅቱ እጅግ ወሣኝ ተልዕኮ ነው። ስለሆነም:-

- በጋራ ራዕይ ዙሪያና በተናበበ መልክ በየአካባቢው ሕዝባዊ ቡድኖችንና ሙያዊ ድርጅቶችን በስፋት በማቋቋም የዐማራውን ወጣት ማንቃት፣ ጊዜያዊና ዘለቄታዊ ጥቅሞቹን ማስከበር፤
- የፖለቲካ ንቅናቄዎችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማቋቋም፣ ከጠባብ ድርጅታዊ ጥቅም አልፈው አገራዊና ሕዝባዊ አመለካከትና ተጠሪነት እንዲኖራቸው ማበረታትና ተግባራዊ እንዲሆን ግፊት ማድረግ፤
- የምንጠቀምባቸው ጊዜውን የዋጁ የትግል ስልቶች አስተዋይነትን፣ አቃፊነትን፣ ተበቃይ አለመሆንን፣ ወሣኝነትንና ቁርጠኝነትን፣ ወዘተ የመሣሰሉ ዐማራዊ አኩሪ መገለጫዎችንና ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በተለይም የዘመኑን ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን እንዲያቅፉ ማድረግ፤ እንዲሁም፣
- ከወሣኙ "የሽግግር ጥያቄ" አኳያ በጥልቅ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ አቋም መያዝ፣ ልዕለ-ግብ አስጨባጭ ትልሞችን መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ አስተማማኝ ፈርጀ-ብዙ የፍኖተ ካርታ ዝግጅቶች ማድረግ ናቸው።

## (4) አስፈላጊ ግብ-አስጨባጭ ስልታዊ ተልዕኮዎች/ግንዛቤዎች

ይኽን አንገት ያስደፋ ሁለ-ገብና ሥር-ሰደድ አደጋ (በተለይም ከጎሣ ግጭት አልፎ ወደ ሐይማኖት ግጭት እየተሸጋገረ የመጣውን ቀውስ) የተገነዘቡ የዐማራ ወጣቶች እራስን ከዳግም ጥቃት ተጋላጭነት ለመታደግ የሚያስችል ማንነቱንና ታሪኩን የሚመጥን ቅድመ-ዝግጅት ለማድረግ በሕዝባዊ እምቢተኝነት መንፈስ መንቀሳቀስ መጀመራቸው እንደ ዘራዊ ንቅናቄ ሣይሆን እንደ ትልቅ የተኅድሶ ምስራች ሊታይ ይገባል። ይኽ "ራስህን አድነህ አገርህን ታደግ" ሕዝባዊ ንቅናቄ መንፈሱም፣ ዓላማውም ተልዕኮዉም ግልጽ ነው። በመሆኑም፣ የዐማራውን ብርቅየ እሴቶች አቅፎ ሊቀጥልና የጅምላ ፍርድንና ኅጠኝነትን በመጠየፍ ማንነቱን የሚመጥን አኩሪ ውጤታማ ሥራዎች ላይ መረባረብ ይጠበቅበታል።

**የዐማራን የጎልውና ጥያቄ ማስከበር ኢትዮጵያዊነትንም ማዳን ነው ስንል ከዘገየ ጎጠኛነት ተነስተን አይደለም።** "ያልጠረጠረ ተመነጠረ፣ ያልተዘጋጀ ተፈጀ" እንደተባለው የምንሞተው ለኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነታችን ነው፣ የሚገድሉን ግን አማራ እያሉ ነው። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ አንገብጋቢ ከሆኑ ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ለአብነት ይጠቀሳሉ፡-

- መንግሥት ዘረኝነት በተጠናወተው ሴራ የዐማራውን የመኖር ዋስትና ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣ ዐማራው እንዳስፈላጊነቱ ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ ራሱን መከላከልና ማዳን መብቱም ግዴታውም ነው፤ከእንግዲህ ሰሚ-ያጣ ብሶቱን፣ ለቅሶውንና አቤቱታውን አቁሞ መሠረታዊ (የሰብዓዊም፣ የዜግነትም) መብቱን በራሱ ጥረት ማስከበር አለበት፤እንዲሁም
- ለዐማራ ሕዝብ ዉክልና አለን በማለት ስልጣን ላይ የተፈናጠጡት ዐማራውን ራሱን በቀዳሚነት እያሳደዱና እያስገደሉ ያሉትን ሳይሆን፣ እኔንና ታሪኬን ሊመጥኑ፣ ተከብረውም ሊያስከብሩኝ ይችላሉ የሚላቸውን ሐቀኛ መሪዎች ያለምንም ተጽዕኖ የመምረጥ መብቱን በትግል መጎናጸፍ አለበት።

የዚኽ ቃልኪዳን ይዘት አጠቃላይ ቢሆንም እንደሁኔታው በሚለዋወጡ የአጭር ጊዜ ስልት /የታክቲክ/ ጥያቂዎችን በተመለከተ ለምሣሌ ያኽል የሚከተሉትን የመሣሰሉ ተግባሮች በአጽንዖት እንዲታሰብባቸው ያስፈልጋል፡-

- የዐማራ ሕዝብ ታሪካዊ የርስት መሬቱ እንዲመለስለት፣ እንዲሁም ይኽን የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የግል ባለቤት መሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንዲጎናጸፉት መታገል፤
- ራስን ለመከላከል በሕግ የተመዘገቡ የግል መሣሪያዎችን የመያዝ መብቱ ሊከበርለት፤ ዐማራን እንደ ዐማራ ለይቶ ለማጥቃት የሰለጠኑ ፀረ-ሰላምና ዘረኛ ቡድኖች/ድርጅቶች ደግሞ ትጥቃቸውን እንዲፈቱ፤
- አዲስ-አበባና ድሬዳዋ ከክልላዊ መስተዳደር ሥርዓት ውጭ መሆናቸው እውቅና አግኝቶ ራሣቸውን-በራሣቸው እንዲያስተዳድሩ ማድረግና የተረኝነት ምዝበራውን ማስቆም፤
- የወልቃይት ጠገዴ፣ ራያ፣ መተከልና ደራ ወደ ነበሩበት ቀድሞዎቹ ክፍለ-አገራት (ጎንደር፣ ወሎና ጎጃም) እንዲመለሱ መደገፍ፤
- የዐማራ ሕዝብ በዓለም-አቀፍ የተደነገጉ ሰብዓዊና የዜግነት መብቶቹ ተከብረው በፈለገበት ቦታ ካለ-አድልዎና ውጥረት በሰላም የመኖርና የመንቀሳቀስ ዋስትና በተግባር እንዲረጋገጥለት፣እንዲሁም
- የዐማራ ክልል በተዓማኒ ሕዝቡ መጠን ልክ የሚገባውን ባጀትና መሰረተልማት እንዲያገኝ ማድረግ የሚሉ ናቸው።

## (5) መዳረሻው ፡-ከአምባገነናዊ ሥርዓትና ከድህነት አረንቋ መውጣት፤አገራዊ አንድነትን ማስቀጠል

በቅርቡ በአረሙማው እኩይ ቡድን በተጠለፈው የማዕከላዊ መንግስት መሪነትና በዐማራ ተበየው የክልላዊ ቡድን አጋፋሪነት በትጥቅ ማስፈታት ስም ሁሉን-አቀፍ ጦርነት በዐማራው ላይ ታውጆበታል።ዐማራው በክልሉም ኖረ በክልሉ ውጭ በማንነቱ እየደረሰበት ያለውን የጅምላ መፈናቀል፣ ዓይን-ያወጣ አድልዖና ዘግናኝ ጭፍጨፋ ማስቆም፣ ለእነዚኽ የወንጀል ድርጊቶች ተጠያቂዎችን ለፍርድ ማቅረብና የሰብዓዊና የዜግነት መብቱን ማስከበር፣ የቅድሚያ-ቅድሚያ የሚሰጠው አጣዳፊ ተልዕኮ ሲሆን፣ የዐማራው መሠረታዊ ጥያቄዎች በዴሞክራሲ ተቋማት አስተዳዳር ስርዓትን መገንባት፣ በብሔራዊ አንድነት ሥር ለዘርፈ-ብዙ አገራዊ ችግሮ ተመሣሣይ ራዕይ ካላቸው

ወገኖች ጋር በመሆን ዘለቄታዊ መፍትኄ ማስገኘት የዐማራው ልዕለ-ግብ ነው። በጥበብና በድፍረት ታግለው ያላገኙትን ዲሞክራሲ በባለቤትነት ለመጎናጸፍ አይቻልም።

**በአገራችንም ሆነ በቀረው ዓለም እንዳየነው ያልተገታ ሥልጣን ማግጠ ቀስ-በቀስ ወደ አምባገነንነት ይለወጣል።** ስለዚህ፣ ዐማራ-ተኮር ድርጅቶች የዘረኛ ሥርዓት አክትሞ ሉዓላዊ ሕዝብ የሚገታው ሕገመንግሥታዊ ሥርዓትን መሠረተ-ድንጋይ ለመጣል ያለው አስተማማኝ አማራጭ አንድ መሆኑን በጥሞና መርምረው ስኬታማ ድርጅቶችን መገንባትና የጠሩ አታጋይ የፖለቲካ አቋሞችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣ ይገባቸዋል። ጠንካራ ዐማራ-ተኮር ስብስቦችና ድርጅቶች እንዲፈልቁ መደገፍና በድህረ ዘውጌ የሽግግር ሂደት ዐማራው እንደ ትልቅ ባለ-ድርሻ ሕዝብ ለድርድር የሚያቀርበውን አጀንዳ በግልጽ መተለም፣ እንዲሁም በሙሉ ቁርጠኝነትና በድፍረት ተልዕኮዎቹን ማራመድና ተዓማኒ መሪዎች ከአብራኩ እንዲወጡ መጣር አንገብጋቢ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል።

ስለዚህ፣ የዐማራው ትግል መዳረሻ አምባ-ገነናዊነት ዘረኝነትንና ድህነትን ከምድረ-ኢትዮጵያ በማጥፋት፣ ፍትኅ የሰፈነባት፣ የዜጎቿ እኩልነት የተረጋገጠባት፣ ጠንካራ መሠረት ላይ የቆመችና አንድነቷ የተከበረ አገር እንድትኖር ማድረግ ናቸው። ለሰፊው ዐማራ ሕዝብ በዐማራነትና በኢትዮጵያዊነት ሁለት እግሮቹ በመሮጥ ራሱን  ማክበርና ማስከበር አማራጭ የሌለው ተልዕኮም፣ ስልትም፣ ልዕለ-ግብም ነው።

- የጎልውና፣የሰብዓዊና የዜጋዊ መብቶቻችንን እንዳስፈላጊነቱ ታግለን እናስከብራለን።
- ከአያቶቻችን የወረስናቸውን የትውፊት አደራዎችና ቅርሶች በፍጹም አንረሳም።
- ፍትኅ ካለትግል ስለማትገኝ አገር ወዳድ ሁሉ ጀምበሯ ሳትጠልቅ ለራስህ ብለህ አብረኸን ቁም።

--------

<u>ዋሽንግተን ዲ.ሲ.፡-</u> ግንቦት 2015 ዓ.ም.

# The Amara Freedom Charter

May 2023

*The Amara Freedom Charter (AFC) distills the nature of the existential threat and historic opportunities facing the Amara of Ethiopia today. It articulates the collective political identity, fundamental interests, enduring challenges, and strategic choices facing such an illustrious but beleaguered people. This manifesto promotes a shared understanding to facilitate collective action. As a historically informed, forward-looking, and defiantly inspiring articulation of the new Amara political consciousness, the AFC is intended to support Amara-focused organizations in crafting coordinated and practicable action plans. This is critical for defending the Amara from the recently declared war against them as a people by the Oromuma/Woyane alliance, and , as importantly, build a free society.*

*The five takeaways from the Charter are as follows: (i) the Amara are a post-tribal, civilizational, people who uphold the rule of law under a strong a multinational State which explains why they as a collective are having such a hard time organizing ethnocentrically; (ii) the Amara are the anchor people of Ethiopian nationalism and the flagbearers of the Ethiopian State. This would explain why they still stand for a united and democratic Ethiopian State and embrace the imperatives of Amara nationalism and Ethiopian nationalism alike; (iii) the Amara, as a defiantly proud people, have been targeted for relentless exclusion, ethnic cleansing, and even genocide by anti-Ethiopian forces at home and abroad since the Italian Occupation; (iv) the Amara stand with all who seek to build an inclusive, citizen-based, democratic constitutional order; and (v) Amara-focused organizations and movements need a manifesto that articulates a self-narrative of shared identity along with a clear vision of the destiny of the Amara as a people. This Charter will, therefore, inspire and facilitate the forging of roadmaps and actionable programs of advocacy and material support for building formidable deterrence to save our people first and then contribute to the building of a democratic and prosperous Ethiopia for all.*

## 1. The Amara in the Context of Ethiopia Today

Ethiopia is a multiethnic and multi-faith society with about 80 ethnolinguistic groups and three major religious traditions—Orthodox Christianity, Sunni Islam, and Indigenous. Two widely intermixed and comparably sized linguistic/identity groups, the Amara and Oromo, comprise two-thirds of the Ethiopian population. Three-quarters of the Amara ethnicity reside in the so-called Amhara Regional State. More notably, they constitute over half of the urban population in the country. Muslims, concentrated in the Wollo region, account for about 15 percent of the Amara population.

The Amara, whose origins are traceable to the "Amhara" districts of today's southwestern Wollo, are among the most pedigreed of Ethiopians:

- They share genealogy with many other groups, including Gurage, Agew, Tigre, Afar, Argobba, and the Oromo.
- They are masters of syncretic blending of the native and the alien—fusing elements of African culture with Judaism, Christianity, and Islam; and extending the reach of Geez by nurturing a hybrid national lingua franca that is Amharic.
- They excel in accommodating and acculturating newcomers to create a civilization out of the cultural mosaic that gave birth to modern Ethiopia.
- They are averse to exclusivist and divisive politics based on ethnicity or religion while embracing the rights to equality and democratic rule.

As a civilizational people and the flagbearer of the modern Ethiopian state, Amara of all faiths and regions profess the following points:

- Amara's core values include trust in God, respect for all humanity, hard work, humility, inclusion, and pride in our *cultural* identity as Amara and *political* identity as Ethiopians.
- The modern Amara vision is to create a democratic government with prosperity and freedom for all citizens, regardless of ethnicity, place of birth, or religion.

The mission that animates and informs the objectives and goals of all Amara-focused civic and political organizations embraces and modernizes the best of our traditions, including a remarkable work ethic that helped develop much of Ethiopia, self-reliance, social solidarity, active engagement in public affairs, accountability of leaders, commitment to the rule of law, and espousal of diversity.

Ethiopia sadly missed the industrial revolution and barely survived the onslaught of European colonialism. This means its subsistence agrarian economy could not support the completion of a robust state and nation-building. The bitter harvest is a polarizing identity-based political mobilization after 1990. The Amara, it turns out, had become the scapegoated victims.

***The Amara are standard-bearers of a world-class cultural identity, which, as an amalgam of the Ethiopian mosaic, is today associated globally with Ethiopiawinnet, a sovereign Ethiopia.*** As a post-tribal cultural group with various genealogies, the Amara have served as the Ethiopian state's flagbearer since the thirteenth century. In being so, this national community has given the country the most cherished icons of inclusivist political identity comprising distinctive forms of Abrahamic religions, dress, cuisine, music, family relations, art, literature, and a lingua franca (Amharic) that is spoken or understood by over 80 percent of Ethiopians. These hallmarks of state and nation-building, albeit too slowly, paved the way toward meritocratic and equitable access to education, civil and military services, business, and justice.

## 2. The Amara Today

Thanks to a polarizing identity-based political mobilization championed over the last four decades by secessionists and other ethnocentric groups, the Amara as a people have been targeted for collective punishment. This relentless persecution has belatedly rattled the Amara society ever since the enshrining of a hyper-ethnicized Constitution in 1995, especially after the Oromo political elite has made it clear that it will follow in the footsteps of the Tigrean political elite in capturing the state and marginalizing the Amara. This state of affairs has inevitably aroused the latent historical angst of Ahmed Gragn's devastating jihad of the sixteenth century, in the aftermath of which the Oromo opportunistically usurped much of the ancestral lands of the Amara, renaming places and forcibly assimilating people.

The alien ideology of revolutionary democracy in vogue today denigrates Ethiopia's historical identity as uniformly oppressive and offers an alternative of ethnocratic self-determination safeguarded by a kleptocratic vanguard Party. This polarizing political order is neither democratic nor revolutionary. The rise of this adventurist radicalism and the we-versus-them ethnocentrism that anchors it have regrettably targeted the Amara as the collective "other." Worse still, the inflammatory rhetoric from the top down depicts the Amara as an "oppressor group" deserving of collective punishment even at the risk of destabilizing the country and rendering the ruling cabal a genocidal pariah in the international community. ***Identarian politics is deconstructing the national fabric and must therefore be eradicated to pave the way for a genuinely democratizing Ethiopia.***

In the name of 'land to the tiller,' the Amara lost their age-old *rist* rights to land to become (like the rest of their compatriots) tenants of the state and have since become the prime target of relentless political and ethnic violence, including widespread internal displacements and genocidal massacres **targeting the Amara.** Furthermore, they have been subjected to ethnic cleansing from cities and districts they founded and lived for generations; demonized in party manifestos and the state and para-state media; their historic provinces have been either annexed or marginalized by design in the allocation of public investment; willfully undercounted in the national censuses; and discriminated in public employment, education, and justice.

The culmination of this avoidable assault is the repeated invasions and wanton destruction of half of the zones of the Amhara Regional State (with well over 15 million citizens) over the past two years. This adventurism by the paramilitaries of the Tigray People's Liberation Front (TPLF) and the Oromo Liberation Front (OLF) has produced nothing but inexplicably mindless carnage and pillage. Bafflingly, this coordinated mix of state and nonstate regional actors has been complemented by the joint operation of the Federal forces and the Oromia regional state militia to disarm Amara citizen militia, with a posture of nothing but self-defense. On the heels of the abandonment of Wollo and northeast Gondar to the TPLF looting and marauding army in the name of "strategic retreat," this so-called "law enforcement operations" is no less than a *de facto* declaration of war on the Amara.

In the face of this relentless and overlapping state-sponsored atrocity crimes, terrorism, and crime against humanity over the past half-century, the Amara have shown remarkable patience and enduring loyalty to the Ethiopian state. This recognition lag is no longer excusable on the grounds of humanity, free citizenship, or political fairness. Furthermore, other Ethiopians have regrettably been too reticent, out of malice or fear, to denounce such outrages against tens of millions of Amara citizens of Ethiopia at the cost of endangering their own freedom. ***The Amara understandably lacked a political tradition of acting as Amara, rather than as Ethiopians, to take a united stand against treasonous domestic enemies.***

The fierce urgency of now in organizing (and more organizing) is self-evident today since all the other major ethnic groups in Ethiopia have established numerous political parties to represent them and armed ethnic militia to press their sectarian interests in the event of an unmanageable civil war. The Amara has, until very recently, been oblivious to the domestic danger facing them as well as Ethiopian unity to muster the foresight and courage to exercise their right and obligation to organize in self-defense. In this toxic and alarming environment, responding with unilateral disarmament and weak representative political organizations, succumbing to paralyzing fear, or praying for better days is nothing but shortsighted, cowardly, and even suicidal.

***Despite boasting an elite that is arguably the best-educated and the most prosperous (but ironically the most insecure) in the country, the Amara peasantry remains arguably the poorest in the country.*** As systematic exclusion is progressively morphing into a palpable mortal threat to their very existence as a people and Ethiopia as we have known it, a determined Amara-centric movement has recently emerged. It is fast becoming a formidable force of civil disobedience and multifaceted political activism whose promise is to save the Amara and all Ethiopians from its implacable enemies—domestic and foreign. This civic disobedience and multifaceted resistance, nonetheless, need to be guided by a principled, inspiring, and coherent vision that informs sound strategies of action.

## 3. The Strategic Imperative

Among the hallmarks of a capable and accountable government are monopoly over large-scale violence and respect for the rule of law that is binding on both the strong and the weak. What has become evident over the past few years in Ethiopia is that regional states have exceeded their authority, with the consent of the ruling party, to go beyond establishing police forces to arm hundreds of thousands of ethnic militia and special forces.

These forces have accumulated enough firepower to effectively challenge the national defense forces (as in Tigray), engage in large-scale ethnic cleansing (as in Oromia and Beni-Shangul Gumuz), or invade neighboring regional states over land disputes or consolidate state power (as in Oromia). The latest and most disturbing manifestation is the extra-legal invasion of the Amhara Regional State by expansionist forces currently underway. The joint federal and Oromia, as well as the Tigrean forces, are engaged in a coordinated **strategy** to incorporate bordering Amara districts and disarm the self-defense citizen-militia (Fanno) in the vainglorious hope of enfeebling the Amara as a political contender.

Selectively disarming the Amara in such an incendiary climate, when other ethnic groups are well-armed, is the surest route to second citizenship and devastating civil war. All signs indicate that the demise of the TPLF-led EPRDF and its replacement by the Oromo-led Prosperity Party will do nothing but deepen the hold of the polarizing ethnocratic political order. National elections that are designed to crown a new group of supremacist ethnocrats will surely trigger pre-and post-election political violence, genocide, and national disintegration. It turns out that this is exactly what happened, especially since November 2020.

It suffices to note here that, even within the flawed Constitution's framework, the citizens of Addis Ababa, Dire Dawa, and the Amhara Regional State have not been allowed to elect their leaders freely. Furthermore, the constitutions of the various regional states (most notably, Tigray, Oromia, Beni-Shangul Gumuz, and Harrari) have blatantly disenfranchised and excluded Ethiopianist groups—most notably, the Amara, the Gurage, Wollega, and other parts of Oromia, and the Gamo. Cities (such as Addis Ababa, Dire Dawa, Nazret, Harrer, Assela, and Awasa) have persistently witnessed state and nonstate political terrorism. Ethnically motivated violence in rural regions (such as Wolkait, Tegede, Derra, Metekel, Raya, Kemisse, and Gambella) are prime examples of genocide. A notable implication of this reality is that Amara-focused organizations must work hard to build a national coalition of all like-minded organizations that promote Amara wellbeing and enduring Ethiopian unity under a democratic order.

The fundamental human, civil, political, and economic rights of the Amara cannot possibly be respected without an overhaul of the exclusionary institutions of identity politics, including the current odious Constitution, which was drafted without the participation of the Amara. Electoral politics in a polarized setting where the state has been fully captured by anti-Ethiopian and predatory political groupings cannot bring lasting peace, justice, or prosperity. This is why all Amara and other democratic organizations must demand an inclusionary "negotiated settlement" of the foundational issues that will finally give birth to a genuinely democratic and prosperous Ethiopia.

***We are not being belatedly ethnicist when we assert that the surest way to save Ethiopia is to protect the Amara.*** The practical implications of the preceding analysis are stark: the strategic posture for Amara rights-oriented organizations in a toxic climate of low-intensity civil war is to insist on nothing less than an all-stakeholder transitional arrangement—a negotiated settlement being the norm for all post-conflict societies. The challenge for Amara organizations today is how best to facilitate the much-needed birth of a legitimate political leadership which can table a bold roadmap and political agenda for an equitable political settlement.

The organizational imperatives of mounting an effective deterrence for such a large community under siege must then include:

- Establishing civic and professional organizations under a shared vision and a uniting umbrella to defend and advance Amara's security, political, and economic interests;
- Establishing political movements and political organizations that are accountable to the people rather than to the urban-based and un-anchored politico-economic class; and

- Adhering to the time-honored and exemplary heritage of the Amara people to mount a united front against all forces that pose an existential threat to the Amara and Ethiopia.

To restore the political representation of the Amara and all other Ethiopianists, an inclusive political settlement must be negotiated. An authentic and authoritative interim parliament must be established, consisting of elected and selected representatives from all woreda-level communities that could reasonably oversee a caretaker government. The transitional parliament will then have the mandate to supervise the dismantling of all control networks imposed by political ethnicism, establish commissions on peace and reconciliation as well as reclamation of stolen public assets, the professionalization of the civil and security services under a caretaker government, geographic re-demarcation of administrative regions, and the drafting of a truly democratic constitution that fits Ethiopian realities.

## 4. The Tactical Imperative

In the meantime, all Amara interest groups, and other Ethiopians of good will must insist on:

- All land must be in private ownership.
- The right to bear arms and defend oneself must be respected, especially given the partisan record of the Federal Government in abandoning Amara and other groups to hostile ethnic special forces and militia based in Tigray, Oromia, and Beni-Shangul-Gumuz regional states.
- The right to select one's political representatives and government administrators.
- The right to self-governance by the chartered cities of Addis Ababa and Dire Dawa.
- Respect for the wishes of the truly native people in the forcibly annexed regions of Wolkait-Humera, Raya, Metekel, and Derra.
- Respect for the internationally recognized rights of the Amara regardless of where they reside in the country.
- The release of an equitable share of the Federal budget to all the regions wherever the Amara reside.
- The right of the Amara to forge strategic alliances of mutual benefit with the Afar, Gurage, and other Ethiopians as well as neighboring countries.

## 5. The Endgame: Amara Freedom from Dictatorship, Marginalization, and Abject Poverty

The immediate challenge is to defend Amara citizens throughout Ethiopia from the unprovoked, genocidal, and opportunistic attacks and dislocations. These coordinated attacks have now taken the form of an all-out campaign against anything Amara by the mafia that had captured federal institutions. Eventually, it is only after establishing a credible transitional administration to oversee the ratification of a new constitution that free and fair elections can be conducted to end ethno-fascist dictatorship for good. As we strive to move from being dreamers to makers of our destiny, we are inspired by the real possibility of richly deserved peace, political and social freedom, and prosperity for all Ethiopians. ***For the sake of justice to the aspirations and historic achievements of the Ethiopianist project, Amara movements must learn to run on two strong legs—an Amara one and an Ethiopian one.***

To achieve these noble goals, the Amara must recognize the fierce urgency of organizing itself effectively to launch a united struggle for self-preservation and provide inspiring leadership to bring all Ethiopians of goodwill back to the national fold of an internationally respected Ethiopia.

** To fight injustice, we must first expose it. Justice is earned, not given.
We intend to fight for our birthright to Life, Liberty, and Prosperity.**

***Issued: Washington, D.C., May 2023.***